# የጥገና ሥራ አደረጃጀት / Organisation of the maintenance

## 1. ዓላማ እና አጠቃላይ ሁኔታ

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ለውሃ አገልግሎት ክፍያ መዋጮ የተደረገው ርብርብ አመርቂ (በመላው ወረዳ 100% የሚጠጋ መዋጮ) ሲሆን የማይካድ ጥገና ለማድረግም ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል።





*እጅግ አመርቂ እና በቂ ጥገና በቁጫ ተከናውኗል*

### 1.1 ያልተሟላ የመከላከል ጥገና

ጥቃቅን የሚመስሉ ነገር ግን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የመከላከል ጥገናዎች የሚባሉ ከዚህ በታች ያሉትን መጠቀስ ይቻላል ፡ ፡-





*ያልተሸፈነ ቧንቧ፣ ነገር ግን ትልቅ ግምት የማይሰጣው(በግራ ያለውን ስዕል ተመልከት) ሆኖ ቧንቧው በተቆረጠ ሰዓት መላ የውሃ ስርዓቱን ሙሉ በሙሉ አገልግሎት እንዳይሰጥ የሚያደርግ ነው(በስተቀኝ ያለውን ስዕል ተመልከት)*





*በሮችን ቀለም አለመቀባት እንደ ትልቅ ችግር ተደርጎ አይወሰድም(በግራ በኩል ያለውን ስዕል ተመልከት) ነገር ግን ከጥቂት አመታት በኋላ ከፍሬሙ እንዲላቀቅ መንስኤ ይሆናል! (ቀኝ በኩል ያለውን ስዕል ተመልከት)*





*የሚያንጠባጥብ፣ ያልተቀየረ የውሃ ፎሴት (በግራ) የሚከተሉትን ችግሮች ያስከትላል። (በቀኝ ያለውን ተመልከት)*

1) *ብዙ ውሃ ማባከን እና የውሃ ማጠራቀሚያውን ባዶ ማድረግ*

2) *የውሃ ቦኖውን ማበላሸት*

3) *ውሃ ለመቅዳት አስቸጋሪ ማድረግን ያስከትላል*

## 1.2 መደበኛ እንክብካቤ ያለማድረግ

አንዳንድ ምንጮች እና የውሃ ቦኖዎች በቦኖ ኮሚቴዎች ጥሩ የሆነ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል።





*በግራ በኩል ያለው ቦኖ ከ15 አመታት በላይ አገልግሎት የሰጠ ሲሆን በቀኝ በኩል ያለው ግን ቅርብ ጊዜ የተሠራ ተቋም ነው።ሁለቱም በማህበረሰባቸው በጥሩ ሁኔታ እንክብካቤ የተደረገላቸው ተቋማት ናቸው።*

*ሆኖም ፣ እንክብካቤ የማይደረግላቸው ተቋማትም ጥቂት የሚባሉ አይደሉም።*





*ይህም የእንክብካቤ ጉድለት በምንጮች ላይ ይስተዋላል።እንደሚታወቀው ምንጮች የውሃ ዋስትናና አለኝታ ስለሆኑ እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል።.*





*ወይም ስዕሉ ከቃላት በላይ የሚናገርለት የውሃ ቦኖውን ተመልከት*

### 1.3 ትኩረት ለሙያዊ ጥገና

**የውሃ ቦኖዎችን በፈቃደኝነት ከመጠገን ልምድ** ሙሉ አቅምን በመጠቀም ወደ ሙያዊ ጥገና ወደ ሚደረግ ልምድ ማሸጋገር፤ **እያንዳንዱን የኔትወርኩ አካላት ሙሉ በሙሉ አገልግሎት ሳያቋርጡ ለማቆየት** ስትራቴጂውን እንደገና መወሰን እና ለሁሉም ተዋናዮች የሥራ ክፍፍል ማድረግን ይጠይቃል።

ይህ ስልት የአስተሳሰብ ለውጥን ያካትታል፤ ይህንን የአስተሳሰብ ለውጥ ለማጠናከር በነበሩ ችግሮች ላይ፣ የውሃ አገልግሎቱን ዘላቂነት ላይ ተግዳሮት በሚሆኑ እና ሁሉም ባለድርሻዎች የበለጠ ሙያቸውን ማጠናከር በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

የመንግስት ባለሞያዎች ትክክለኛ ስርዓቶችን በመከተል በተደራጀ መንገድ የበለጠ መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል።

የውሃ ተጠሪዎች ሙሉ የቧንቧ መስመሮችን ለመፈተሽ እና በሁሉም የውሃ ኔትዎርኮች ውስጥ ያሉ ችግሮችን መፍታት ስለሚኖርባቸው በርካታ ተጨማሪ ስራዎች ማከናወን ይጠብቃቸዋል። የውሃ ተጠሪ ማካካሻን በተመለከተ የአሰልጣኙ ሚና ቀድሞ ያለውን አስተሳሰብ መቀየር ሊሆን ይገባል። ውጤታማ ሥራ ተገቢ ማበረታቻ ሊታጀብ ያስፈልገዋል።

## 2. ፍቺዎች፡-

በዚህ ሰነድ ውስጥ (ሌላ ቦታ ካልተገለጸ በስተቀር) የዞኑ ባለሞያ የዞ/ው/መ የተቋማት አስተዳደር ባለሞያ ሲሆን እና የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ የ የወ/ው/ጽ/ቤት የተቋማት አስተዳደር ባለሞያ ተብሎ ይጠራሉ።

### 2.1 ፍተሻ

የውሃ ተቋማትን ችግር/እንከን መለየት፣የውሃ ተቋማትን ደህንነት ሁኔታ እና ሁለንተናዊ ቁመና ለመፈተሽ የተዘጋጀ ቼክሊስት በመጠቀም የተቋሙን ችግር/እንከን መለየትና ቅጹን(ቼክሊስቱን) መሙላት። ይህ የፍተሻ ሥራ የሚጠናቀቀው በየዓመቱ **በጥቅምት** ወር ሲሆን ለተቋሙ የሚያስፈልገውን(ለዘላቂና አስተማማኝ የውሃ አገልግሎት) የማስተካከያ ሥራ የሚታወቀው /የሚለየው ፍተሻውን መሠረት አድርጎ ነው።



ችግሮችን ለመለየት ጥሩ ነው።

*መፍትሄዎችን ለመለየት ግን ጥሩ አይደለም*

**2.2** *የማስተካከያ ሥራዎች*

በፍተሻው የተለዩ ችግሮች እንዲቀረፉ መከናወን የሚገባቸው *ሥራዎች፣*

| ቀበሌ_________ | | የማህበር ስም_________________ | የጥቅምት ፍተሻ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| በፍተሻ የተገኘ ችግር | መደበኛ እንክብካቤ ለውጦች ያስፈልጋቸዋል | አስፈላጊ የማስተካከያ ሥራዎች ያሰፈልጋል | የ"B" ችግር | | የ"C" ችግር |
| | | | ውማ | የውተ/ ወማፌ | ግንበኛ |
| የተቋም አይነት እና ስም(ከላይ በኩል ካለው የቧንቧ መስመርን አካቶ): <u>የጨጨራ በኖ</u> | | | | | |
| ወለሉ ንጹህ አይደለም | ☒ | የየቀኑን ጽዳት ስራ ማደራጀት | ☒ | ☐ | ☐ |
| በኖው ላይ ስንጣቆ አለ | ☒ | የበኖውን የላይኛውን ክፍል መስበርና በፎረምወርክ ማጠናከር | ☐ | ☐ | ☒ |

*የማስተካከያ ሥራዎች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ-*

- ቴክኒካል ይዘት ያለው ድርጊት ሊሆን ይችላል

ለምሳሌ ያልተቀበረ እና ያልተሸፈነ የቧንቧ መስመር ካለ = ቧንቧ የተጋለጠበት ቦታ ላይ ካብ መገንባት እና አፈር ማልበስ

- መደበኛ እንክብካቤ፣ የተዘረጋውን ሥርዓት መፈተሽ እና ሥርዓቱን ማስተካከል ሊያስፈልግ ይችላል።

ለምሳሌ ችግር፡የውሃ ቦኖውና አካባቢው በጣም ቆሸሾ ተገኝቷል። ማስተካከያ ሥራ = የቦኖ ዕለታዊ ጽዳት ማድረግ

**2.3 መደበኛ እንክብካቤ ሥራዎች**

የውሃ ተቋሙ እንከን አልባ አገልግሎት እንዲሰጥ አስፈላጊ የሆኑ እና አስቀድመው የታወቁ በመደበኛነት እና በተደጋጋሚ መከናወን የሚገባቸው ሥራዎች ናቸው (በየቀኑ፣በየሳምንቱ፣በየወሩ ወ.ዘ.ተ)።





**2.4 የመደበኛ እንክብካቤ ሥርዓት ሰንጠረዥ**

ለእያንዳንዱ የመደበኛ እንክብካቤ ሥራ የማከናወን ኃላፊነት የተሰጣቸውን ግለሰቦች እንዲሁም እያንዳንዱ ሥራ ግዴታ መከናወን ያለበትን ድግግሞሽ በዝርዝር የሚገልጽ፣ የሚያስቀምጥ የአሠራር ሥርዓት ሠንጠረዥ ነው።ይህ ሰንጠረዥ ለእያንዳንዱ የውሃ ተቋም ምንጭ እና የውሃ መቅጃ ቦኖ መዘጋጀት አለበት።

| | | | የሥራው ባለቤት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጥራት ላለው የመከላከል ጥገና የሚሰራ ሥራ | የድግግሞሽ መጠን(በወር/በዓመት)-ትክክለኛ ቀን | ስሞች | የቦኖ ኮሚቴ | ውማ | ውተ |
| አጥር እና የአጥር በር መጠገን | እንደአስፈላጊነቱ (በትንሹ በዓመት አንዴ) | | ☐ | ☐ | ☐ |
| ቁጥቋጦ ማስወገድ | እንደአስፈላጊነቱ (በትንሹ በዓመት አንዴ) | | ☐ | ☐ | ☐ |
| የውሃ ጡቶችን ማጥበቅ ወይም የውተ በመጥራት ጡቱን መቀየር | በቋሚነት | | ☐ | ☐ | ☐ |
| በኖና የከብቶች ገንዳ ማጽዳት | በየቀኑ | | ☐ | ☐ | ☐ |

**2.5 የማስተካከያ ሥራዎች ውሳኔ ማሳወቅና ስምምነት**

የውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ፌዴሬሽን በዓመታዊ የውሃ ተቋማት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ሊፈጽም ያቀዳቸውን የማስተካከያ ሥራዎች ውሳኔዎች ዝርዝር ለወረዳ ውሃ ጽ/ቤት በጽሑፍ በማቅረብ ስምምነት መፈጸም አለበት። በጽሑፍ የሚቀርበው ዝርዝር የፌዴሬሽን ህጋዊ ማህተም እና የሰብሳቢው ወይም የተወካዩ ፊርማ ያረፈበት መሆን አለበት።

### 2.6 የB የማስተካከያ ሥራዎች፡-

ማንኛውም የማስተካከያ ሥራ በውሃ ተጠቃሚ ማህበር፣በውሃ ተጠሪ ወይም በፌዴሬሽን አቅም መፈታት የሚችል ከሆነ የ"B" ማስተካከያ ሥራ ይባላል።

ፌዴሬሽኖች በሥራቸው ያሉትን ሁሉንም የ "B" ማስተካከያ ሥራዎች በዓመቱ የጥገና ጊዜ ሠሌዳ ሳያልፍ የማከናወን እና የማጠናቀቅ ግዴታ አለባቸው።እንዚህ የ "B" ማስተካከያ ሥራዎች "B" ወይም "C" ተብሎ በተሰየሙ የውሃ ቦኖ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ።

አንድ የውሃ ቦኖ ቢያንስ አንድ "B" የማስተካከያ ሥራ ተብሎ የተለየ ሥራ በራሱ በቦኖ ሆነ ከፍ ብሎ ባለ መስመር ወይም ግንባታ ካለ ያ ቦኖ "B" ተብሎ ይሰየማል።

| ቀበሌ__________ | | የማህበር ስም__________________ | የጥቅምት ፍተሻ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| በፍተሻ የተገኘ ችግር አሰያየም | ወቅታዊ እንክብካቤ ለውጦች ያስፈልጋቸዋል | አስፈላጊ የማስተካከያ እርምጃዎች | የቢ ችግር | | የሲ ችግር |
| | | | ውጫ | የውተ/ወ ማፌ | ግንበኛ |
| የተቋም አይነት እና ስም(ከላይ በኩል ካለው የቧንቧ መስመር አካቶ): <u>የጩጩራ ቦኖ</u> | | | | | |
| ወለሉ ንጹህ አይደለም | ☒ | የየቀኑን ጽዳት ስራ ማደራጀት | ☒ | ☐ | ☐ |
| በኖው ላይ ስንጣቆ አለ | ☒ | የውሃውን የላይኛውን ክፍል መስበርና በፎረምወርክ ማጠናከር | ☐ | ☐ | ☒ |

### 2.7 "C" ማስተካከያ ሥራዎች

አንድ የማስተካከያ ሥራ የ"C" ማስተካከያ ሥራ ተብሎ የሚሰየመው የማስተካከያ ሥራው ግዴታ የተመዘገበ የሥራ ተቋም ቀጥተኛ ተሳትፎ ግዴታ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው።

አንድ የውሃ ተቋም ቢያንስ አንድ "C" የማስተካከያ ሥራ ተብሎ የተለየ ሥራ በራሱ በቦኖ ሆነ ከፍ ባለ መስመር ወይም ግንባታ ካለ ያ ቦኖ "C" ቦኖ ተብሎ ይሰየማል።

| ቀበሌ__________ | | የማህበር ስም__________________ | የጥቅምት ፍተሻ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| በፍተሻ የተገኘ ችግር አሰያየም | ወቅታዊ እንክብካቤ ለውጦች ያስፈልጋቸዋል | አስፈላጊ የማስተካከያ እርምጃዎች | የቢ ችግር | | የሲ ችግር |
| | | | ውጫ | የውተ/ወ ማፌ | ግንበኛ |
| የተቋሙ አይነት እና ስም(ከላይ በኩል ካለው የቧንቧ መስመር አካቶ): <u>የጩጩራ ቦኖ</u> | | | | | |
| ወለሉ ንጹህ አይደለም | ☒ | የየቀኑን ጽዳት ስራ ማደራጀት | ☒ | ☐ | ☐ |
| መዋቅሩ ላይ ስንጣቆ አለ | ☒ | የውሃውን የላይኛውን ክፍል መስበርና በፎረምወርክ ማጠናከር | ☐ | ☐ | ☒ |

### 2.8 የጥገና መውደቅ

የጥገና መውደቅ ማለት በአንድ ፌዴሬሽን ውስጥ በጥቅምት ወር የ"B" ማስተካከያ ተብለው ከተለዩት ቢያንስ አንድ የማስተካከያ ሥራ እስከ ሚያዚያ 30 ድረስ ሳይጠናቀቅ ሲቀር ነው።



የሚከተሉት ችግሮች፦

- ያልተቀበረ የቧንቧ መስመር/በበቂ ሁኔታ በአፈር ያልተሸፈነ የቧንቧ መስመር
- ያልተቀበረ የፈሳሽ ማስወገጃ ቧንቧ
- ቀለም ያልተቀባ በር
- የሚያንጠባጥብ ወይም በአግባቡ የማይሰራ ፎሴት

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ችግሮች በጥቅምት ፍተሻ ወቅት መለየት ያለባቸው እና የማስተካከያ ሥራዎች ሊታቀድ ይገባል። ከነዚህ ችግሮች አንዱ እንኳን ማስተካከያ ሥራ ሳይከናወን ሚያዚያ 30 ከደረሰ ፌዴሬሽኑ በጥገና ሥራ እንደወደቀ ይቆጠራል።ያልተጠናቀቀ የጥገና ሥራ = የጥገና መውደቅ

### 2.9የሚሠራ የውሃ ተቋም

አንድ የውሃ ተቋም የሚሠራ ነው ሊባል የሚችለው ተቋሙ ንፅህናው የተረጋገጠ በቂ እና የማይቆራረጥ የውሃ አገልግሎት የሚያቀርብ ከሆነ ነው።

ንፅህናው የተረጋገጠ ሊሆን የሚችለው ምንጩና የምንጩ ዙሪያ መሠረታዊ የመከላከያ እና የጥበቃ መሥፈርቶች የሚያሟላ እና ቦኖው ውሃ የሚሰጥ ሲሆን ነው።





ከላይ ያሉት ሁለቱም ተቋማ በጥሩ ሁኔታ ላይ ያሉ አይደሉም . ይሁን እንጂ ምንጩ መሰረታዊ አገልግሎት እየሰጠ ነው

(አንዴ የምንጩ ሽፋን በፌፌዴሬሽኑ ከተሰራ) ቦኖው ውሃ ሊሰጥ ይችላል።

ስለዚህ ከላይ የተገለጹ ሁለቱም ተቋማት የሚሠሩ ተቋማት ሊባሉ የሚችሉት የውሃ ተጠቃሚዎች ከእነዚህ ተቋማት አመታዊ መዋጮ ማዋጣት ሲችል እና በዚህም መዋጮ ፌዴሬሽኑ በራሱ አቅም የማስተካከያ ሥራ መሥራት ሲችል ብቻ ነው።





በተቃራኒው ደግሞ ከላይ የተጠቀሱ የውሃ ተቋማት የማይሠሩ ተቋማት ሊባሉ የሚችሉት

- ምንጩ የውሃ አገልግሎት የማይሰጥ እና የምንጩ ዙሪያም የመከላከያ እና የጥበቃ መሥፈርቶችን የማያሟላ ሲሆን
- ቦኖው ውሃ የማይሰጥ እና ጥገናውም ከፌዴሬሽን አቅም በላይ ሲሆን ነው።

የዚህ መልሶ ግንባታ ሥራ እንደ አዲስ ግንባታ የሚታሰብ እና ትልቅም የሆነ እንቬስትመንት የሚፈልግ ስለሆነ በውድድር ውጤት መስፈርት መሠረት ፌዴሬሽኑ አሸናፊ ሆኖ ሲገኝ መልሶ ግንባታው ሊሠራ ይችላል።

### 2.10 የውሃ ተቋማት ደረጃ ፤

የውሃ ተቋማት ደረጃ የሚያመላክተው የተቋሙን የፍተሻ ውጤት እና የማስተካከያ ሥራውን አተገባበር የሚያመላክት ነው።

**ጥንቃቄ** ፡- የውሃ ደረጃ በራሱ በቀጥታ ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ለማወቅ የሚረዳ አይደለም። ምን መደረግ እንዳለበት ለማወቅ የማስተካከያ እርምጃ አተገባበር ያስፈልጋል ።

### 2.11 የውሃ ቦኖ ደረጃ “A”፡

**የሚሠራ** የውሃ ቦኖ ሆኖ

- በጥቅምት የፍተሻ ወቅት ምንም የማስተካከያ ሥራ የማያስፈልገው ቦኖ ነው።

በአብዛኛዎቹ ኔትውርኮች ላይ ተደጋጋሚ ጥገና ስለሚያስፈልግ በዚህ ቦኖ ደረጃ ያሉ ቦኖዎች አጠራጣሪ ስለሆኑ በሚገባ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

- ወይም እነዚህ ሁሉም ቦኖዎች ከጥር እስከ ሚያዚያ ባሉት ጊዜያት የማስተካከያ ሥራ የተሠራላቸው ተቋማት ሊሆኑ ይገባል።

### 2.12 የውሃ ቦኖ ደረጃ “B”፡

**የሚሠራ የውሃ ቦኖ ሆኖ** በጥቅምት ፍተሻ ወቅት ቢያንስ አንድ የB ማስተካከያ ሥራ ያለው እና ምንም የጥገና ሥራ ያልተሠራለት ቦኖ ነው።

### 2.13 የውሃ ቦኖ ደረጃ “C”፡

በፍተሻ ወቅት **ቢያንስ አንድ C የማስተካከያ ሥራ ያለው** እና ጥገና ያልተደረገለት ቦኖ ነው።

### 2.14 የውሃ ቦኖ ደረጃ “D”፡

**የማይሰራ** የውሃ ቦኖ ነው።

## 3. ካላንደር

| ወር | ተግባራት | ፈጻሚ | ዘዴ |
|---|---|---|---|
| ጥቅምት | የፍተሻ ቼክሊስት፣ የማስተካከያ እርምጃ ምንነት እና የቦኖ ደረጃ አሰጣጥ | የውሃ ተጠሪ እና ወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ | WS3-M11 |
| ኅዳር | ለውማፌ እና ለውማ ተወካች የማስተካከያ እርምጃውን ማሳወቅ<br>የማስተካከያ እርምጃውን ለመስራት የተሳትፎ ፈርማ | ውማፌ እና ወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ | |
| ታኅሳስ | የፍተሻ እና የማስተካከያ እርምጃ ትክክለኛነት በናሙና ማረጋገጥ | ዞን እና አርአያ | WS3-M17 |
| ጥር | የጥገና እቅድ<br>የመደበኛ እንክብካቤ ሥራን ማደራጀት እና ፈር ማስያዝ | የውሃ ተጠሪ እና ወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ | WS3-M14<br>WS3-M13 |
| ከጥር እስከ መጋቢት | በወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ መደበኛ ክትትል ጥገናውን ማካሄድ(የመጨረሻ የጊዜ ገደብ መጋቢት 30) | የውሃ ተጠሪ እና ውማ (የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ ቴክኒካል ድጋፍ) | WS3-M16 |
| ሚያዚያ | በወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ የማስተካከያ እርምጃ ሪፖርት ትክክለኛነት ማረጋገጥ<br>እስከ ሚያዚያ መጨረሻ ድረስ 100% የቢ ማስተካከያ እርምጃ እና ጥገናን ሙሉ በሙሉ ማጠናቀቅ | ወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ | |
| ግንቦት | የማስተካከያ እርምጃ እና መደበኛ እንክብካቤ ትክክለኛነት በናሙና ማረጋገጥ(ምንጭ እና ቦኖ) | ወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ | WS3-M18 |
| ሰኔ | የማስተካከያ እርምጃ መሰራቱን በናሙና ማረጋገጥ | ዞን እና አርአያ | |

| | |
|---|---|
| | *በዚህ ቀለም የተጠቀሱት፣ የትግበራ ቅደም ተከተል ናቸው : መንግስትና አርአያ የመስክ ሰራተኞችን መደገፍ ይጠበቅባቸዋል* |
| | *በዚህ ቀለም የተወከሉት፣ ሥራዎች መፈጸማቸውን የማረጋገጥ ቅደም ተከተል የሚያሳዩ ሲሆኑ የሚከናወኑትም በመንግስት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እና አርአያ ጥምረት ነው* |

ከላይ ባለው የቀን መቁጠሪያ ውስጥ የተዘረዘሩት የእንቅስቃሴዎች ዘዴዎች በእነዚህ ሰነዶች ውስጥ ይገኛሉ-

**መሰረታዊ ፍተሻ፣ የማስተካከያ ሥራ እና ተሳትፎ**

- Doc n° WS3-M11 “Initial Diagnostic, corrective measure & Engagement”

**መደበኛ እንክብካቤ ዘዴ**

- Doc n° WS3-M13 “Periodic Care Methodology”

**የጥገና እቅድ ዘዴ**

- Doc n° WS3-M14 “Maintenance Plan Methodology”

**የጥገና ክትትል እና ድጋፍ**

- Doc n° WS3-M16 “Maintenance follow-up & support”

**የፍተሻ ማረጋገጫ**

- Doc n° WS3-M17 “Diagnoses Validation”

**የማስተካከያ ሥራ ማረጋገጫ**

- Doc n° WS3-M18 “Corrective Measure Validation”

## 4. አስተሳሰብ ለውጥ መፍጠር እና ማሰልጠን

ዓላማው በቀጥታ ኃላፊነት ላለው ሰው (የውሃ ተጠሪው) እና ቀጥተኛ ደጋፊ / ተቆጣጣሪው (የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ) ከጥገና ጋር የተዛመዱ ተግባራትን በትክክል የመተግበር **ቴክኒካል አቅም እና** የባለቤትነት ስሜት በመፍጠር ወደ አንድ የጋራ ዓላማ ( **አስተሳሰብ** ) ማምጣት ነው።

ቀዳሚ ዓላማው የውሃ አገልግሎትን ዘላቂነት ማረጋገጥ ሲሆን በቀጣይ የጥገና ወጪዎችን በመቀነስ በተቻለ መጠን የተሻለውን ጥገና በመደበኛነት ማከናወን ነው። ሁሉም የታቀዱ የፍተሻ እና የማረጋገጫ ሂደቶች ይህንን ዓላማ ለመደገፍ እንደ ዘዴ የሚያገለግሉ መሆን አለባቸው.

ባለድርሻ አካላት የፌዴሬሽኑን ውጤት ለመጨመር ብለው የኔትዎርክ ችግሮችን ችላ ብለው ካዩ ይህ ወደ ኔትወርክ ውድቀት ሊያመራ ይችላል። በአንፃሩ ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንደ ተቆጣጣሪ እና እንከን ፈላጊዎች (ማለትም ድጋፍ ሳይሰጡ እስኪ.ወድቁ ከጠበቁ) አድርገው ካዩ ለፌዴሬሽኖች አቅም ካለመፍጠራቸውም በተጨማሪ ተስፋ ሊያስቆርጡ ይችላሉ።



*ይህ በምስሉ ላይ የሚታየው ሸጥ እንዲሁ እንደዋዛ ቸል የሚባል ከሆነ በምንጭ ሳጥኑ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል።*



የግንዛቤና የቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ የድጋፍ ሞጁሉ ሲዘጋጅ የቢሮ እና የመስክ ተግባራዊ ልምምዶችን ማካተት ይኖርበታል።

### 4.1 በቢሮ ውስጥ የሚሰጥ ስልጠና;

ሀ. በአንድ ዓላማ ላይ የጋራ የሆነ አቋም መያዝ (በተለይ የአስተሳሰብ ዝንፈትን በማስወገድ ላይ ማተኮር)- ለምሳሌ የተሳሳተ ዝንባሌ በማንሳት ማብራሪያ መስጠት

ለ. ስለጠቅለላው የሥራ ሂደት (የጊዜ ሰሌዳ) መገንዘብ እና በሂደቱም የደረስንበትን ደረጃ ማወቅ

ሐ. ስለሥራ ሂደቱ ማብራራት( **የቲዎሬቲካል ቴክኒካል** እውቀት) - ተግባራቱ ከዚህ በታች ባለው ዝርዝር ተብራርቷል

**ይጠንቀቁ ፡** በቢሮ ላይ የተመሰረተ ስልጠና በጭራሽ በቂ አይደለም! ሰዎች እንቅስቃሴውን በትክክል እንዲረዱ በተግባር ሰርቶ ማሳየት ሁል ጊዜ አስፈላጊ ነው።





### 4.2 የመስክ ሥልጠና፡

ልክ የመስክ ደረጃ ፈፃሚዎች በመስክ እንደሚፈጽሙት፤ በመስክ ላይ ያለውን ሂደት በትክክል ይለማመዱ፣ አሰልጣኙ ሥልጠና የሚሰጠው የሚከተለውን ለማስተላለፍ ያለመ ሊሆን ይገባል።

- **ተግባራዊ የቴክኒክ ችሎታዎች** (ለምሳሌ፡ ተግዳሮቶችን ማየት መቻል) - **ድርጅታዊ አካሄድ** (ለምሳሌ፡ መፍትሄዎችን ለማግኘት በጋራ ማሰብ መቻል) - **የቁርጠኝነት አስተሳሰብ** (ለምሳሌ፡ ሙሉውን ሂደት መከተል)

**ደጋፊ አስተሳሰብ** (የበለጠ ልምድ ያላቸው ባለሞያተኞች ጀማሪዎች ተገቢውን አስተሳሰብ እስኪይዙ እና እስኪቀበሉ ድረስ አብረው በመሆን እና በማሰልጠን መደገፍ)




የመስክ ልምምዱ(ሰርቶ ማሳየት እና ሥልጠና) ምንም እንኳን ረጅም እና ብዙ ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም አቋራጭ መንገድ መከተል አያስፈልግም። ዋናው አሰልጣኝ አቋራጭ መንገድ ከተጠቀመ፣ የመስክ ሠራተኞች የጥገና ፕሮቶኮሉን ለመጣስ ዕድል/ነፃነት ያገኛሉ። ⇒ አቋራጭ መንገድ መከተል ውጤቱ ዝቅተኛ ጥራት ደረጃ ያለው ጥገና ያስከትላል።




ለእያንዳንዱ ተግባር፣ ሥልጠናው መጀመር ያለበት በከፍተኛ ደረጃ ከሚያስተባብሩ አካላት በተዋረድ እስከ ፈጻሚዎች ድረስ ሊሆን ይገባል።ሙሉው ቅደም ተከተል 4 ደረጃዎችን ይዟል።

- **ደረጃ 1** (1 የቢሮ እና 1 የመስክ ክፍለ ጊዜ ለየዞኑ)

የ ክልሉ ግብረ ኃይል እና አርአያ ማስተባበሪያ

→ የ ዞን ግብረ ኃይል አስተባባሪ፣ የዞኑ ባለሞያ፣ የ አርአያ ዞን ባለሙያ

- **ደረጃ 2** (1 የቢሮ እና 1 የመስክ ክፍለ ጊዜ ለየወረዳ)

የዞኑ ባለሞያ እና የ አርአያ ዞን ባለሙያ

→ ወረዳ ማኔጅመንት ቡድን፣ ሁሉም የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ እና የአርአያ ባለሞያ

- **ደረጃ 3** (1 የመስክ ክፍለ ጊዜ በየወረዳው ባለሙያ)

የአርአያ ባለሞያ እያንዳንዱን የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሞያ በመጀመሪያው የፌዴሬሽኑ ድጋፍ ወቅት በጋራ ይሠራል።

- **ደረጃ 4** (1 የቢሮ እና 1 የመስክ ክፍለ ጊዜ በየፌደሬሽኑ)

የወ/ው/ጽ/ቤት ባለሙያ በመጀመሪያው የልምምድ ተግባራቸው የውሃ ተጠሪዎችን ይደግፋሉ

